# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP

ሰኔ 4 ቀን 2005 ዓ.ም.

### የወያኔ አገዛዝ ሕዝብን ለጦርነት፤ ሀገርን ለጥቃት እያዘጋጀ ነው

የወያኔ አገዛዝ የሕዝብን ትኩረት መደረግ ካለበት ወሳኝ ትግል ለመነጠል ሲያደርገው የነበረውን ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ በተመክሮ የተገነዘበው ነው። በቅርቡ ደግሞ ህዳሴ ግድብ በሚለው ማታለያ የለመደባቸውን ተላላዎች በዙሪያው እያሰለፈና ሕዝብንም እየዘረፈ ያለው አልበቃ ብሎት ግብጽን እየተነኮሰና እየቀሰቀስ በመቀጠሉ የአባይ ውሀ አንድም ጠብታ አይቀነሰብኝም ከምትለው ከስግብግቧ ግብጽ ጋር ጦርነትን እየጋበዘ ነው።

ኢትዮጵያና ሌሎች ሀገሮች በነጭና ጥቁር አባይ የመጠቀም መብታቸው የተጠበቀ መሆኑ አያከራክርም ። በአለም አቀፍ ህግ መሰረትም ሌሎች ከወንዞቹ ተጠቃሚ ሀገሮች ውሃ እንዳያገኙ ማድረግ የሚፈቀድ አይደለም። አባይን በተመለከተ ተንኮለኛው የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሱዳንና ግብጽን ብቻ ይዞ የወሰነው የውሀ ድርሻ/ክፍፍል ትክክለኛ አለመሆኑም አከራራክሪ ኣይደለም--ግብጽና ሱዳን አሌ ቢሉም። ግብጽ በረሀዋን ልታለማና ሚሊዮኖችን ልታሰፍር በመፈለግ የአባይን ውሀ በተጨማሪ ደረጃ መፈለጓና የተፋሰስ ሀገሮችን ጥቅም ከቶም አላዳምጥ ማለቷም የሚደገፍ አይደለም ። ወያኔ በአሁኑ ጊዜ  ትልቅ ግድብ በሌለ ገንዘብ እሰራለሁ ብሎ የተነሳው ለኢትዮጵያ አስቦ (ወያኔና የኢትዮጵያ ጥቅም ሆድና ጀርባ ናቸውና) ሳይሆን የሕዝባዊ አመጽ ነፋስ ወደ ሀገራችንም እንዳይነፍስ በሚል የህዝብን እይታ ለማደናገር የሸረበው ተንኮል መሆኑ ክርክርን አይጠይቅም ። በኢትዮጵያ እስከዛሬ የተሰሩት ግድቦችና ገና ያላለቀው ግልገል ጊቤ ቁጥር ሶስትንም ጨምሮ ለሀገሪቷ የመብራት ሀይል ፍጆታ ከበቂ በላይ ሆነው ሳለ ዛሬም በብዙ ከተሞች መብራት በፈረቃ እየተሰጠ እንዳለ ሕዝባችን የሚያውቀው ነው። ግዙፍ ግድብ ለመገንባት መነሳትና ይህንንም ግብጽ እንደምትቃወም እየታወቀ በስልት ጉዳዩን በመያዝ ፈንታ ድንፋታና ፕሮፓጋንዳን ማስቀደሙ፤ ቦንድ ብሎ ሕዝብን ማስጨነቁና ማስገደዱ፤ ሀገር ወዳድ መስሎ ለመቅረብ መፍጨርጨሩ ሕዝብን ሊያደናግር የሚችል አይደለም። የለመዳባቸው የወያኔ የገደል ማሚቴዎችና አደናጋሪዎች --በባድሜ ጦርነት እንዳየነው ሁሉ-- ሀገር ልትጠቃ ነው ኡኡ በሚል ወያኔን በመታገል ፈንታ ሕዝብ እንዲደግፍና ከጎኑ እንዲሰለፍ ለማድረግ ከወዲሁ የተንኮል ቅስቀሳ፤ የማደራጀት ስራና ጫጫታ ጀምረዋል። ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ይህንን በሚገባ ተገንዝቦ ውጉዝ ከመ አርዮስ መባል አለባቸው።

የግብጽ ሕዝብ ጠላታችን አይደለም። አንዋር ሳዳት  የአባይ ወንዝ ከተገደበብን ጦርነት የግድ ይሆናል ያለውንም አንረሳውም--ዛሬም የግብጽ መሪ ተመሳሳይ አቅዋም በመውሰድ እሱም በበኩሉ ልክ እንደ ወያኔ ውስጣዊ ውጥረቱን ዘወር ለማድረግ ይፈልጋል። ተጨባጭ ሁኔታውንና አቅምን ሳያውቁ ሳይመዝኑ ህዳሴ ግድብ ይሰራል ብለው ጫጫታ ላይ ያሉት ክፍሎች ቅዠት ላይ ናቸው ። ከግብጽ ጋር ጦርነት ቢነሳ ይህ የኢትዮጵያ ሳይሆን የወያኔ ነው - ልክ እንደ ባድሜ። 130 ሺ ዜጋ አልቆ ምን ተገኘ? ወያኔና አጫፋሪዎቹ--አንዳንዶቹ ደግሞ ተቃዋሚ ነን ሲሉም ይጥራሉ--

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 2**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP*

ኢትዮጵያ በአባይ ልትጠቀም ስትነሳ በግብጽ ተጠቃች ወይም ልትጠቃ ነው በሚል ሀገር ወዳድ ሁሉ ተነሳ ለማለትና ለማደናገር አቅደዋል። የሚሞኙላቸው አይኖርም ማለትም አይቻልም። ለነገሩ ግብጽ ኢትዮጵያን ሊወር አይችልም-- አይሮጵላኖች አስነስቶ ግድብ ተብየውን ሊደበድብ ይችላል። የሚያቆመውም አይኖርም ። ዕድሜ ለወያኔ ስንት ሚሊዮን ብር የፈሰሰበትን አየር ሃይል በትኖ በጀሌዎቹ ሞልቶት ይቀልዳል። መካላከያ ተብየው ሆኖ ሕዝብንም ከፋፍሎና አሽመድምዶ ይገኛል ። ኢትዮጵያ መብቷን ለማስከበር አቅም የላትም። ወያኔ የአሜሪካ ሎሌና ተገዢ ነው-- አሜሪካ ደግሞ ግጭት ከተነሳ ግብጽን መቃወም ኣንችልም/ ብላ ለወያኔ አስጠንቅቃለች። የወያኔ አገዛዝ ከድጡ ወደ ማጡ ሊከተን ነው እየጣረ ያለው። ይህን መቃወም ደግሞ ለሀገራችን ደህንነት ወሳኝ ነውና ወያኔና ቅጥረኞቹን ወግዱ እረፉ እንበላቸው።

ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ከግብጽ ጋር ግጭቱ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥት የለም ። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ከግብጽ ጋር ተፈራርሞ የሀገርን ጥቅም መሸጡንም መርሳት አንችልም። ወያኔ ጫካ ሳለም በግብጽ መረዳቱንና የተከዜ ድልድይን ሊያፈርስ መሞከሩንም የምንረሳው አይደለም። ወያኔ ከስረ መሰረቱ ሀገርን ለባዕድ ሻጭ ጻረ ኢትዮጵያ ሀይል ነበረ--አሁንም ነው ። ለዚህም ነው ከባዕድ ጋር የፍጥጫን ጎዳና መርጦ ሀገራችንን ለጥቃት ሊያጋልጥ እየተፍጨረጨረ ያለው። በዚህ ጻረ ኢትዮጵያዊ ጉዞው ሀገር ወዳድ ዜጎች ከቶም መቸም ልናጅበው አይገባም ። በባድሜ የወደቁ ዜጎቻችን አጥንት ያወግዘናል።

በአባይ ስም አገርን ለማስጠቃት ወገንን ለማዘናጋት የታቀደውን ወያኔያዊ ሴራ በአንድነት ልናወግዝ ይገባል።

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email** **ESPIC@aol.com**
**Website** **WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 2**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**